2014-10-26

# ፍርሃት የገደለው!!



በቁሙ እየሞተ

ሁሌ እየዋተተ

አንደበቱን ዘግቶ፣

በአካል ውስጥ ናኝቶ፣

ፍርሃት በሱ ገብቶ፣

ደነዝ ካደረገው፣

እያዶለደመው

ዝምታ ገደለው፣

ዝምታ ቀበረው፣



ሲገደል ዝም፣

ሲሞት ዝም፣

ሲታሰር ዝም፣

በሱ ላይ አምጿ ክብሪት ከጫረበት፣

ንዳድ አንድዶበት፣

ባሪያ አድርጎ ሊገዛው፣

እሱን ካስገበረው፣

ድሩን ካደራበት፣

ጉልበቱን ጨርሶ አቅሙን ከበላው፣

ባሃሳብ አጉላልቶ ቡክን ካደረገው፣

ላዩን ቆሞ የሚሄድ ነፍስ ያለው ቢመስልም፣

እንኳን ለሃገሩ ለራሱም አይሆንም።

እሱ የበደነ መሆንን እያወቅን ፣

የወንዜ ልጅ ጀግና

ያገሬ ልጅ ጅግና

ፍርሃቱን ቀብረህ ጎበዝ ወገን አድን፣

ፍርሃቱን ቀብረህ ጎበዝ ወገን አድን።

መይሳው ከምድረ ስዊድን